# የቤተ ክርስቲያን ማሳሰቢያ

### የአርብ ፕሮግራም

በአርብ ፕሮግራም እግዚአብሔር ግሩም የጸሎትና የትምህርት ጊዜ እየሰጠን ነው። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎትና ቃሉን በመማር እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ወገኖችም መሪዎችን ማነጋገር ትችላላችሁ። ጌታ ይባርካችሁ።

### የልጆች አግልግሎት ቀን

በOctober 27 በሚኖረው የሕሁድ አገልግሎት ልጆቻችን አዋቂዎችን የሚያገለግሉበት እለት ነው። በዚህ እለት ስለሚኖረው ፕሮግራም እየጸለይን እንድንቆይ እናሳስባለን። የተለየ ግሩም ግዜ ስለሚኖረን በዚህ ፕሮግራም ሁላችንም እንድንካፍለ እናበረታታለን።

### እርስ በርስ እንተያይ

ባለፈው ሳምንት የጀምርነውን ለሌሎች ወገኖቻችን የመደወል እና እርስ-በእርስ የመጠያየቁን ነገር አጥብቀን እንድቀጥል ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። በዚህ አገልግሎት እየተጋችሁ ያላችሁ ወገኖች እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

"ወደ ውጭም አውጥቶ:- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አላቸው።
እነርሱም:- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት:-
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)
630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)
773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)
773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)

**መደበኛ ፕሮግራሞች**
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

Chicago Yemsrach Evangelical Church

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2:10

# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!




"ወንዙም በሚመጣበት ያለው ሁሉ በሕይወት ይኖራል።"
(ሕዝ. 47:9)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

**October 6, 2019** | **መስከረም 25፤ 2012 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| **ጸሎት ..........................** | ወንድም ዘሪሁን ዳዊት |
| **አምልኮ..........................** | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| **ፕሮግራም መሪ ............** | ወንድም ረድኤቱ ካሳ |
| **ቃል ...............................** | ወንድም ጸደቀ ጴጥሮስ |
| **ማጠቃለያ .....................** | ፕሮግራም መሪ |

## <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

"ይህን ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሣው ለዚህም ነገር እኛ ሁላችን ምስክሮች ነን፤ ስለዚህ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ብሎና የመንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል ከአብ ተቀብሎ ይህን እናንተ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው።"
(ሐዋ. 2:32-33)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| **ወ/ም አያሌው አሰፋው** | **ማክሰኞ** | **5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640** |
| **እህት ሰናይት ከበደ** | **ማክሰኞ** | **7319 N Oakley Ave, Chicago, IL 60645** |
| **ወ/ም ጌቱ ጳውሎስ** | **ማክሰኞ** | **7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660** |
| **ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ** | **ማክሰኞ** | **7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645** |
| **ወ/ም ረድኤቱ ካሳ** | **ሃሙስ** | **7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631** |
| **ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ** | **ሰኞ** | **9107 Laramie St. Skokie, IL 60077** |
| **ወ/ም ዮናስ ባህሩ** | **ማክሰኞ** | **5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640** |
| | | |

# መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### መንፈስ ቅዱስ የትንሳኤው ምስክር።

*"ከበዓሉም በታላቁ በኋለኛው ቀን ኢየሱስ ቆሞ፡- ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ። በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ፥ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ። ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ፤ ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና።" (ዮሐ. 7:37-39)*

ባለፈው ሳምንት እንዳየነው መንፈስ ቅሱስ የጌታ ኢየሱስን ማንነትና አዳኝነት ይመሰክራል። በዛሬው መልዕክት ደግሞ መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስ የክርስቶስ ትንሳኤ ምስክር እንደሆነ እንመለከታለን። ጌታ ኢየሱስ በላይ የሰፈረውን ቃል የተናገረው የዳስ በዓል የመጨረሻና ታላቁ ቀን ላይ ነው። የዳስ በአል የደስታና የምስጋና በአል ነው። እስራኤላዊያን ይህንን በዓል የሚያከብሩት መክር ከሰበሰቡ በሁኋላ አምላካቸውን በደስታ ለማመስገን ነው። (ዘዳ. 16:15) ልምላሜንና ፍሬአማነትን ለማመልከት ዳስ ሰርተው ዳሱን በለመልሙና ፍሬያማ በሆኑ ቅጠሎች ይቸፉኑታል። (ዘሌ. 23:39) ከዛም በአምላከቸው ፊት ሰባት ቀን ደስ ይላቸዋል። (ቁ.40) የበዓሉ የመጨረሻ ቀን በዓሉ በብዙ ምስጋና የሚጠናቀቅበት የደስታ ጥግ ያለበት የሃሴት ቀን ነው። በዚህ የበዓሉ ቁንጮ ቀን ኢየሱስ ቆሞ በታላቅ ድምጽ ጮሆ "ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ" ሲል አወጀ። ከበዓሉ አውድ አንጻር ይህ ግር የሚል ነገር ነው። በዚህ የዳስ በዓል የመጨረሻ ቀን ጥማት ያለ አይመስልም፤ ከዛ ደስታ ያለፈ ምንም ነገር ያለ አይመስልም። ነገር ግን ኢየሱስ የሚበልጥ ነገር፤ ያልተደረሰበት ነገር ለተጠሙ ሁሉ የሚሰጥ የከበረ ስጦታ እንዳለ አበሰረ።

ይህ የከበረ ስጦታ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው። ኢየሱስ እንደገለጸው መንፈስ ቅዱስ በኛ ውስጥ "የሕይወት ውኃ ወንዝ" ነው። ይህ ወንዝ ከሰማይ ምንጭ ሳያቋርጥ የሚፈስ ሕይወትን የሚሰጥና የሚያድስ ምንጭ ነው። ምንጩ በውስጣችን ነው። ከውስጣችን እየፈለቀ ወደ ውጪ ይፈሳል። ሲፈስ ደግሞ ልምላሜንና ህይወትን እየሰጠ ይፈሳል። ይህ ሃሳብ በሕዝቅኤል 47 ላይ ከምናነበው በቤተ መቅደሱ ውስጥ ከሚወጣው ውሃ ጋር ይመሳሰላል። ልክ የመንፈስ ቅዱስ ወንዝ ከሆዳችን እንደሚፈልቅ ውሃው የሚወጣው ከመቅደሱ ውስጥ ነው። የውሃው ኃይል እየጨመረ እንደሚሄድ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስም ስራ በሕይወታችን እየበዛና እያደገ የሚሄድ ነው። ውሃው በሚያልፍበት ሁሉ ልምላሜና ሕይወት እንደሚሆን ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በሚሰራበት ሁሉ ፈውስና ሕይወት ይሆናል። ኢየሱስ የዚህን የአዲስ ኪዳን ተስፋ ትልቅነትና ብልጫ ለማጽናት ቆሞ፣ ጮሆ ተናገረ። ማናችንም ቸል ልንለው የማይገባን ታላቅ ስጦታ ነው። መንፈስ ቅዱስን ሁልጊዜ፣ በየቀኑ መጠማት አለብን።

ቢዚህ ክፍል የወንጌሉ ጸሐፊ ሐዋሪያው ዮሐንስ ጌታ በዚህ ስፍራ የተናገረው በእርሱ የሚያምኑት ሊቀበሉት ስላለው ስለ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ያብራራል። ደግሞም "ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበር" ይለናል። ክፍሉ መንፈስ ቅዱስ የተሰጠን ኢየሱስ ስለከበረ እንደሆነ ያስረዳናል። ይህንን ደግሞ በሐዋ. 2 ላይ ከተጻፈልን ጋር አገናኝተን ስናነበው የኢየሱስ መክበር በትንሳኤ መነሳቱ እንደሆነ እንገነዘባለን። በሐዋ. 2:32-33 ላይ ሐዋሪያው ጴጥሮስ የኢየሱስን ትንሳኤ ከመንፈስ ቅዱስ መምጣት ጋር አገናኝቶ ሰበከ። "ይህን ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሣው ለዚህም ነገር እኛ ሁላችን ምስክሮች ነን፤ ስለዚህ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ብሎና የመንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል ከአብ ተቀብሎ ይህን እናንተ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው" ይለናል። ወገኖቼ፡- የአብ ተስፋ የሆነውን መንፈስ ቅዱስን ለቤተ ክርስቲያን የላከው ሞትን አሸንፎ በትንሳኤ ከፍ ከፍ ያለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ኢየሱስ በታላቅ ትንሳኤ ባይነሳ ኖሮ መንፈስ ቅዱስ አይመጣም ነበር። ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ የመጣው ኢየሱስ ስለከበረና ይህንኑ እውነት ለመመስከር ነው። ስለዚህም መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስን ትንሳኤ ይመሰክራል።